# ***የ EEPCO Millennium Bond ለመግዛት ጠቃሚ መረጃ***

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በውጭ ሀገር ለሚገኙ ኢትዮጵያዊያንና በትውልድ ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የውጭ ሀገር ዜጐች ብቻ የሚሸጥ የውጭ ምንዛሪ ቦንድ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን (EEPCO Millennium Bond) አውጥቷል፡፡

በውጭ ሀገራት የምገኙ ኢትዮጵያዊያንም ሆኑ በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ ሀገር ዜጐች የ EEPCO Millennium Bond በሚኖሩበት ሀገር ከሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲ- ች ኃና የኮንሱለር ጽ/ቤቶች በመቅረብ መግዛት ይቻላል፡፡

1. የቦንድ ሽያጭ ዋና ዓላማ

   የቦንድ ሽያጩ ዓላማ የኮርፖሬሽኑን የፋይናንስ አቅም ከማጐልበት በተጨማሪ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጲያዊያን ቦንድ በመግዛት በአገራቸው ኖየተካሄደ ባለው የልማት ኖንቅስቃሴ ተሳኖፊ በመሆን ራሳቸውን ጠቅመው ለሀገራቸው ኖድገትና ብልጽግና የበኩላቸውን ድርሻ ኖንዲያበረክቱ ማድረግ ነው፡፡

2. የቦንዱ ይዘት

   - የቦንዱ ዓይነት- ኮርፖሬት ቦንድ
   - ቦንዱን ያዘጋጀው - የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኖይል ኮርፖሬሽን
   - ወኪል - የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
   - የቦንዱ ስም - ኢ.ኤ.ኖ.ኮ ሚሌኒየም ቦንድ
   - ክፍያው የሚከናወነው - በዶላር፣ በፓወንድ ስተርሊንግ፣ ዩሮ ኖና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሚገበያይባቸው ሌሎች የውጭ ሀገር ገንዘቦች ይሆናል፡፡
   - የብቁነት መስፈርት- በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልድ ኢትዮጵያውያን ብቻ ቦንዱን ለመግዛት ብቁ ናቸው፡፡
   - ዝቅተኛው የቦንድ ዋጋ - 500 የአሜሪካን ዶላር ሲሆን ከዚህ በላይ መግዛት ለሚፈልጉ በመቶ ብዜት (100፣ 200፣ 300 ....) ኖያሉ በመቀጠል የሚፈልጉትን ያህል ተጨማሪ ቦንድ ያለገደብ መግዛት ይችላሉ፡፡
   - የቦንዱ የጊዜ ገደብ- 5፣7 ኖና 10 ዓመት ይሆናል፡፡

- ቦንዱ የሚያስገኘው ወለድ- ባንኩ 5 ዓመት የጊዜ ገደብ ላለው ቦንድ 4%፣ 7 ዓመት የጊዜ ገደብ ላለው ቦንድ 4.5% ኖና 10 ዓመት የጊዜ ገደብ ላለው ቦንድ 5% ወለድ በየዓመቱ ይከፍላል::
- ቦንዱ የሚከፈልበት ጊዜ - የቦንዱ የጊዜ ገደብ ሲያበቃ ይሆናል::
- ወለድ የሚከፈለው- በየዓመቱ ይሆናል::
- ዋስትና- መንግሥት ለቦንዱ ሙሉ ዋስትና ሰጥቶና ል::
- ተጨማሪ ጥቅም - ይህ ቦንድ ሀገር ውስጥ ለሚጠየቅ ብድር በዋስትናነት ያገለግላል::
- የገቢ ግብር - ከቦንዱ ግዢ የሚገኝ የወለድ ገቢ ከግብር ነፃ ነው::

**2. ቦንዱን ለመግዛት አማራጭ መንገዶች**

EEPCO Millennium Bondን በሦስት አማራጮች መግዛት ይቻላል::

**2.1 በአካል በሀገር ቤት በመገኘት መግዛት ይቻላል::**

**2.2** ከሚኖሩበት ውጭ ሀገር ሆነው በቀጥኖ የቦንዱን ክፍያ በመፈፀም መግዛት ይችላሉ:: ይህኛውን ለመግዛት በሦስት የገንዘብ ማስተላለፍ ዘዴ ሊጠቀሙ ይችላሉ::

ሀ. የክፍያውን ገንዘብ በቀጥኖ በባንኩ- በኩል በስዊፍት ኮድ/ SWIFT/ በመጠቀም ወደ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በማስተላለፍ፣

ለ. በሐዋላ ድርጅቶች በኩል ገንዘቡን በማስተላለፍ ክፍያ መፈፀም (የሀዋላ ድርጅቶችን ዝርዝር ለማግኘት ኖዚህ ኖጫኑ፣)

ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር የሚሠሩ የሐዋላ ድርጅቶች ዝርዝር

- ዌስተርን ዩንየን የሐዋላ አገልግሎት
- ኢ.ኤም.ቲ የሐዋላ አገልግሎት
- አር ስፒድ ሬሚኖ ንስ
- አትላንቲክ ትራንስፈር
- ሳሪ ኤክስቼንጅ
- አላሙዲ ኤክስቼንጂ
- ዘንጂ ኤክስቼንጂ
- ብሪቱ ትራንስፈር
- አማል ትራንስፈር
- ደሊል ትራንስፈር

ሐ. ቦንድ ገዥው በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ ባንኮች በአንዱ በከፈቱት የውጭ ምንዛሪ ሂሳብ ተቀናሽ በማድረግ ክፍያውን በመፈፀም፣

2.3 በሀገር ቤት ሕጋዊ ውክልና በመስጠት በተወካያቸው አማካይነት መግዛት ይችላሉ::

3. ቦንዱን ለመግዛት የሚያስፈልጉ ሠነዶች

3.1 ቦንዱን በአካል በሀገር ቤት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመገኘት ለመግዛት የሚፈልጉት ማሟላት ያለባቸው ሠነዶች

ሀ. በትክክል የተሟላ ኖና በቦንድ ገዥው የተፈረመ የማመልከቻ ቅጽ፣

ለ. ገንዘቡን በመያዝ ወደ ሀገር ገብተው ከሆነ በኤርፓርት ዲክሌር የተደረገበት ማረጋገጫ ሰነድ፣/ዲክሌራሲዮን/

ሐ. ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የኢትዮጵያ ፓስፖርትና የመኖሪያ ፈቃድ ኮፒ

መ. በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆነው የውጭ አገር ዜግነት ላላቸው ዜግነት የወሰዱበት አገር ፓስፖርትና የኢትዮጵያዊነት ማረጋገጫ መኖወቂያ

ሠ. አንደ ጉርድ ፎቶግራፍ / ፖስፖርት ሳይዝ/

3.2 ውጭ ሀገር ሆነው በቀጥኖ ገንዘቡን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለዚሁ አገልግሎት በተከፈተው የኢ.ኤ.ኖ.ኮ ሂሳብ ቁጥር 02702-17976800 በማስተላለፍ መግዛት የሚፈልጉ ከሆነ መሟላት ያለባቸው ሠነዶች:

ሀ. ለመግዛት ያሰቡትን የቦንድ መጠን ያህል ገንዘቡን በተጠቀሰው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ያስተላለፉበት ደረሰኝ ዋና ኮፒ

ለ. በትክክል የተሟላ ኖና በቦንድ ገዥው የተፈረመ የማመልከቻ ቅጽ/ ማመልከቻውን ለማግኘት ኖዚህ ይጫኑ /

ሐ. ኢትዮጵያዊ ለሆኑ የኢትዮጵያዊያነት ፖስፖርትና የመኖሪያ ፈቃድ ኮፒ

መ. በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው ከሆኑ ዜግነት የወሰዱበት አገር ፖስፖርት ኖና የኢትዮጵያዊነት ማረጋገጫ መኖወቂያ / ቢጫ ካርድ/

ሠ. አንድ ጉርድ ፎቶግራፍ/ ፖስፖርት ሳይዝ/

3.3 ቦንዱን በሀገር ቤት በሚገኝ ሕጋዊ ተወካይ አማካይነት ለመግዛት የሚፈልጉት መሟላት ያለባቸው ሰነዶች

ሀ. በሚኖሩበት ሀገር ከሚገኘው የኢትዮጵያ ሚሲዮን የሚያስፈልጉትን ፎርማሊቲ- ች በማሟላት የተፈፀመ የውክልና ማረጋገጫ ሰነድ

ለ. በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመቅረብ በቦንድ ባለቤቱ ስም ተሞልቶ የተፈረመ የቦንድ ግዥ ማመልከቻ

ሐ. የቦንድ ገዥው የኢትዮጵያዊነት ማረጋገጫ ፖስፖርትና ሕጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ ኮፒ

መ. በትውልድ ኢትዮጵያዊ ሆነው የውጭ አገር ዜግነት ላላቸው ዜግነት የወሰዱበት አገር ፖስፖርት ኖና የኢትዮጵያዊነት ማረጋገጫ መኖ ወቂያ ኮፒ

ሠ. የቦንድ ገዥው አንድ ጉርድ ፎቶ ግራፍ / ፖስፖርት ሳይዝ/

ረ. ገንዘቡ በሰው የሚላክ ከሆነ ያመጣው ሰው ወይም የሚያመጣው ሰው ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ለኤርፖርት ጉምሩክ አሳውቆ የተቀበለው ዲክላራሲዮን ፣

4. ቦንድ ማስተላለፍን በተመለከተ

ይህ ቦንድ አስፈላጊ መረጃ- ች ተሟልተው ሲቀርቡና ገዥው ሲስማማ የብቁነት መስፈርት ለሚያሟላ ሁለተኛ ሰው ሊተላለፍ ይችላል::

5. የወለድ ክፍያን በተመለከተ

የወለድ ክፍያ የሚፈፀመው በውጭ ምንዛሪ ወይም በወቅቱ በሚኖረው የውጭ ምንዛሪ ተመን ወደ ኢትዮጵያ ብር ተቀይሮ ሲሆን ወለዱ በገዥ- ች ምርጫ መሠረት፣

- በግንባር በመቅረብ ወይም በሕጋዊ ወኪል በኩል በብር ለመክፈል፣
- በውጭ ምንዛሪ በሚከፍቱት ሂሳብ ገቢ ለማደረግ፣
- ወደ ውጭ ሀገር ለማስተላለፍ፣
- ሌላ ተጨማሪ ቦንድ ለመግዛት ወይም
- ከውጭ ለሚገቡ ዕቃ- ች ክፍያ ለመፈፀም ሊጠቀሙበት ይችላሉ::

6. የቦንድ የጊዜ ገደብ ሲደርስ

የቦንዱ የጊዜ ገደብ ሲደርስ የቦንዱ ዋጋ በገዢው ምርጫ መሰረት

- በውጭ ምንዛሪ ሊከፈለው፣
- በውጭ ምንዛሪ በሚከፍተው የባንክ ሂሳብ ገቢ ሊደረግለት፣
- ሌላ ተጨማሪ ቦንድ ሊገዛበት ወይም
- ከውጭ ለሚገቡ ኖቃ- ች ክፍያ ለመፈፀም ወዘተ... ሊጠቀምበት ይችላል::

7. ገንዘቡ የሚተላለፍበት የሂሣብ ቁጥር ውጭ ሀገር ሆነው በቀጥኖ ገንዘቡን በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለዚሁ አገልግሎት በተከፈተው የኢ.ኤ.ኖ.ኮ የሂሣብ ቁጥር 02702-17976800 ማስተላለፍ ይቻላል::

8. ተጨማሪ ማብራሪያ ከፈለጉ በሚከተሉት የስልክ ቁጥሮ በመደወል መጠየቅ ይቻላል::

1. ***202 364 6389***
2. ***202 274 4565***
3. ***202 274 1862***
4. ***202 274 4561***
5. ***202 274 6388***
6. ***202 274 4555***